የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ኔትወርክን መጠቀም ሙብት  ነው። የአውታረ መረብ መለያዎን ለመጠቀም ከዚህ በታች ያሉትን የአውታረ መረብ ደንቦች ለመከተል ማንበብ እና መስማማት አለብዎት።

የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የኮምፒዩተር እና የኢንተርኔት አገልግሎትን ለተማሪዎች ያቀርባል። በበይነመረብ በኩል ተማሪዎች የውሂብ ጎታዎችን(databases)፣ ድረ-ገጾችን እና አንዳንድ ጊዜ የኢሜል አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። ተማሪዎች በመስመር ላይ ማተምም ይችላሉ። ተማሪዎች ኮምፒውተሮችን እና ኢንተርኔትን በሃላፊነት እና ከትምህርት ቤት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች ብቻ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ኔትወርክን መጠቀም ሙብት ነው። የአጠቃቀም ሁኔታዎችን መጣስ ሙብቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በዲስትሪክት ሰራተኞች እንዲወሰድ ሊያደርግ ይችላል። ሁሉም ሌሎች ተዛማጅ የተማሪ ፖሊሲዎች ተፈጻሚዎች ሲሆኑ ሌሎች መዘዞች እንደ መታገድ ወይም መባረርን ጨምሮ ሊከተሉ ይችላሉ። እባኮትን "የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መሰረታዊ ህጎች" መመሪያ መጽሐፍን ይከልሱ።

የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የኢንተርኔት አገልግሎትን ለመጠቀም ባለኝ ሙብት መሰረት፣ የሚከተሉትን ተረድcie ተስማምቻለሁ፡

የኮምፒዩተር ሃብቶችን በኃላፊነት እጠቀማለሁ።

- በይነመረብን፣ ኢሜል እና ሌሎች የኮምፒውተር ግብዓቶችን ለአካዳሚክ ተግባራት ብቻ እጠቀማለሁ።
- በአስተማሪዬ ወይም በቤተመጽሐፍት ባለሙያ የተፈቀዱ ትምህርታዊ ጨዋታዎችን ብቻ እጫወታለሁ።
- በመምህሬ ወይም በትምህርት ቤት የተቀመጠውን የህትመት መመሪያዎች እከተላለሁ።
- ለትምህርት አገልግሎት ተስማሚ የሆኑ ቁሳቁሶችን ብቻ ነው የማቆየው።
- ጸያፍ፣ ጨዋነት የጎደለው፣ ትንኮሳ፣ ስም የሚያጠፋ ወይም ሌላ አፀያፊ ነገር በምንም መልኩ አላስተላልፍም ወይም ሆን ብዬ አላደርስም።

የኮምፒውተር ሃብቶችን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እጠቀማለሁ።

- ስሜን፣ ሥዕሌን፣ አድራሻዬን፣ ኢሜሌን ወይም ሌላ በግል የሚለይ መረጃን በመስመር ላይ አልሰጥም።
- የውይይት ክፍል፣ የማስታወቂያ ሰሌዳዎችን፣ ብሎጎችን ወይም  ኢንተርኔት ድረ-ገጽ ላይ መጫን በአስተማሪ ፈቃድ ብቻ እገለገላለሁ።
- የይለፍ ቃሌን ለታመኑ አዋቂዎች ብቻ ነው የማጋራው ፡፡ የሌላ ሰው የይለፍ ቃል አልጠቀምም።

- የድር ማጣሪያዬን አላመልጥም ወይም የበይነመረብ እንቅስቃሴዬን አልደብቅም።

የኮምፒውተር ሃብቶችን በአክብሮት እጠቀማለሁ።

- ሆን ብዬ በኔትወርኩ ወይም በበይነ መረብ ላይ ያለውን መረጃ ለመጉዳት ወይም ለማጥፋት አልሞክርም፡፡
- የኮምፒውተር መሳሪያዎችን አላበላሽም።
- ፍቃድ ሳልጠይቅ የኮምፒዩተር ቅንጅቶችን አልቀይርም።
- የሌሎች ተማሪዎችን ፋይሎች፣ መረጃዎች ወይም መቼቶች አልቀይርም።

የሌሎችን አእምሯዊ ንብረት በሚያከብር መልኩ የኮምፒዩተር ሃብቶችን እጠቀማለሁ።

- ያልተፈቀዱ ሶፍትዌሮችን ወይም ቁሳቁሶችን አልጭንም፣ አላከማችም ወይም አላሰራጭም።
- እራሴን የፈጠርኩትን ስራ አስረክባለሁ/አቀርባለሁ። ከሌሎች ምንጮች ከወሰድኩ እነዚህን ምንጮች በትክክል እጠቅሳለሁ።
- ስለ ሌላ ሰው አሉታዊ፣ ጎጂ፣ ሀሰት ወይም አነጋጋሪ ይዘትን ጨምሮ፣ በመላክ፣ በመለጠፍ ወይም በማጋራት በሳይበር ጉልበተኝነት አልሳተፍም።

የሚከተሉትን ተረድቻለሁ፥

- በኮምፒውተሬ እና በኔትዎርክ አካውንቴ ለሚደረገው ነገር ተጠያቂ ነኝ።
- የዲስትሪክት ሰራተኞች በዲስትሪክት ኮምፒዩተር ወይም በዲስትሪክት በተሰጠው የኔትወርክ አካውንት በኩል የተላከ፣ ወይም የደረሱትን ነገሮች የመገምገም መብት አላቸው።
- የትምህርት ቤት ዲስትሪክት ሰራተኞች በዲስትሪክት ኮምፒዩተር ላይ የተከማቹትን የመመርመር መብት አላቸው። እነዚህን ውሎች እና ሁኔታዎች በመቀበል፣ በዲስትሪክት ኮምፒዩተር ወይም በዲስትሪክት የተሰጠ የአውታረ መረብ መለያ በመጠቀም ለተፈጠሩ፣ ለተላኩ፣ ለመገኘት ወይም ለተከማቸ ነገር የግላዊነት ወይም ሚስጥራዊነት መብትን እተወዋለሁ።
- የዲስትሪክቱ ሰራተኛ ህገ-ወጥ፣ ጸያፍ፣ ትንኮሳ ወይም አላስፈላጊ ሊሆን ይችላል ብሎ ያመነውን ማንኛውንም ነገር ማረም ወይም ማስወገድ ይችላል።
- ዲስትሪክቱ የኢንተርኔት አገልግሎት ተግባራት እርስዎ የሚፈልጓቸውን ልዩ ልዩ መስፈርቶች እንደሚያሟሉ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ከስህተት የፀዳ ወይም ያልተቋረጠ እንደሚሆን ቃል አይገባም፡፡
- የዲስትሪክት ፖሊሲዎችን፣ የፌደራል እና የክልል ህጎችን ለመጣስ የኮምፒውተር ሃብቶችን አልጠቀምም።

- የኢንተርኔት ፖሊሲዎችን መጣስ ምን እንደሆነ የትምህርት ቤት ዲስትሪክት አስተዳዳሪዎች የመጨረሻ አስተያየት አላቸው።

ጥሰቶች ከላይ በተዘረዘሩ ብቻ የተወሰኑ አይደለም፡፡በስምምነት ሰነዱ ያልተዘረዘሩ ጥሰቶችም ያካትታል።